# አንድ አማራ ሲገደል ሙቶ ፋኖ ይወለዳል

ነሐሴ 14 ቀን 2015 ዓም(20-08-2023)በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ የቀረበ ትንታኔ

ግፍና በደል በሰፈነበት ቦታ የሕዝብ ትግል ይወለዳል።ያንን የሕዝብ ብሶትና በደል ለማስገድ የሚታገል የሕዝብ እምባ ጠባቂ፣ሙብት አስከባሪና ለጥቃት ፈጥኖ ደራሽ ወይም ደም መላሽ የሆነ ቆፍጣና እምቢ ባይ ይነሳል።ያን የተነሳ ሕዝባዊ ሃይል የሚያሸንፈው ሃይል ፍጹም አይኖርም፤ሕዝብ ተሸንፎ አያውቅምና!፣ምንም እንኳን ውጣ ውረዱ ቢበዛም ትግሉ የማታ ማታ በሕዝቡ አሸናፊነት ይጠናቀቃል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት ከተጫነበት የጭቆናና የግፍ ቀንበር ለመላቀቅ ብዙ መስዋእትነት ከፍሏል።በትግሉ ሜዳ አንዳንድ ብልጣብልጦች ብቅ እያሉ ትግሉን ጠልፈው ተጠቅመውበታል።ደርግ የተባለ የወታደሮች አምባገነን ስብስብ 17 ዓመት ያሻውን ሲያደርግ፣ሲገል፤ ሲያሳድድ ኖሮ በመሰል ጉልበተኛ በጎሰኞች ቡድን ሥልጣኑን ተቀምቶ ኢትዮጵያን ለአፍራሾቿ አስረክቦ ተበታተነ። መሪው በነጮች በተለይም በአሜሪካኖች ምክርና ድጋፍ የሚኖርበት ቦታ ተመቻችቶለት የነበረችዋን እንጥፍጣፊ የአገር ሃብት ካዝና ሰብሮ ይዞ ወደ ዙምባብዌ ፈረጠጠ።በዛም የተመቻቸ ኑሮውን እስከዛሬ ድረስ በመምራት ላይ ነው።ለሠራው ወንጀልና የአገር ክህደት የጠዬቀው የለም። ምክንያቱም የጨፈጨፈው አገር ወዳዱን ስለሆነ ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ብለው አቅፈውት ኖረዋል።እዚህ ላይ ነው በነጮች ዓይንና አስተሳሰብ ኢትዮጵያውያን ጠላት፣ ህይወታቸውም ዋጋ ቢስ ሆኖ መወሰዱ በገሃድ የታወቀው።ለዚህ አቋማቸው ምክንያት የሆነው ደግሞ ኢትዮጵያ ድንበሯን አልፋ ሌሎች አገሮችን በመውረሯ ሳይሆን ከቅኝ ገዥዎች መዳፍ ውስጥ ሳትገባ ፣ የመጣውን የነጮች ወራሪ አሳፍራ በመመለሷና ለሌሎች የቅኝ ግዛት ስር ለወደቁ አገሮች የነጻነት ምልክት ሆና በመገኘቷ ነው።በፊት ለፊት መጥቶ ያልተሳካለት የውጭ ወራሪ ሃይል በውስጥ ሰርጎ በመግባት ኢትዮጵያን በእጅአዙር ቅኝ አገዛዝ ለማንበርከክ የጎሳ ፖለቲካ ንድፈሃሳብ አስታጥቆ ከሃዲ ባንዳዎችን ኢሕአዴግ በሚል ጭንብል በትግራዮች ተገንጣይ ቡድን ዙሪያ አዘጋጅቶ፣አስታጥቆና መርቶ ለሥልጣን ያበቃው የዛሬ 32 ዓመት ነበር።

ኢትዮጵያን ከማዳከም ዓላማው ኤርትራ ተገንጥላ የየባሕር በሮች እንዳይኖራት በማድረግ የአገር መናዱን ሥራ ሀ ብሎ ጀመረው። ወያኔ የተባለ እኩይ ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን አጃቢ የጎሳ ስብስቦችን አስከትሎ አገሪቷን እንዲቆጣጠር አደረጉ። እስከዛሬም ድረስ ይኸው አገር አጥፊና ጸረ ሕዝብ የጎሰኞች ስብስብ ተግባሩንና ዓላማውን ሳይቀይር በዬጊዜ መልኩንና ስሙን እዬቀያዬረ ዕድሜውን ለማራዘም እንዲችል ያላሰለሰ ድጋፍ አድርገውለታል።አሁንም እያደረጉለት ነው።ለዚያም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ከውጭና ከውስጥ ጠላቶቹ ጋር የሚያደርገው ትግል ነው የምንለው።

የጎሰኞቹ አገር አጥፊው ቡድኖች ምንም እንኳን ኢትዮጵያን በማፈራረሱ ላይ አንድ ዓላማ ቢኖራቸውም ተገንጥለው ለሚመሰርቱት አካባቢ አቅም ግንባታ በሚያደርጉት የኤኮኖሚና የመሬት ዘረፋ ግብግብ ላይ የሕዝቡ ትግል ተጨምሮበት ወያኔ ከሥልጣን መንበሩ ተወግዶ ያሳደገው የአነግ የበኩር ልጅ ኦሕዴድ ክፍተቱን እንዲጠቀም በተሠራው አሻጥር የለውጥ ሃይል መስሎ ብቅ አለ።አብይ አህመድ የተባለውን የወያኔ ጆሮ ጠቢና ሰላይ ከፊት አሰልፎ በሚረጨው ፕሮፓጋንዳ ለጥቂትም ጊዜ ቢሆን ሕዝቡን አወናበደው።መሪና መካሪ ድርጅት የሌለው ሕዝብ በግለሰቡ በሚረጨው ባዶ የቃላት

ጨዋታ ደነዘዘ።እስከነጭራሹ ሙሴያችን እያለ አዝማሪው በዘፈን፣ ኪነተኛው በተውኔቱ፣ጸሃፊው በግጥምና በቅኔ ጋዜጠኛው ሙያውን ዘንግቶ የሥርዓቱ ቃል አቀባይ ሆነ።፣የሃይማኖት አባት ነኝ ባዩ ሳይቀር በድርሳነ ገድሉ ከፈጣሪ የተላከ መለኮታዊ ሃይል እስኪመስል ድረስ ሰግዶ ማጨብጨቡን ተያያዘው።ለጥቅምና ለሥልጣን የቋመጡት ምሑራን ሳይቀሩ የለውጥን ትርጉም አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ሕዝቡን የአብይ ስርዓት ተሸካሚ እንዲሆን ግንባር ቀደም ሰባኪያን ሆኑ ፣በአጭሩ የጥፋት ሃይሉ፣ የኦነግና የወያኔ ስርዓት ደቀመዛምርት ሆኑ።ያም ሆኖ ግን የሥርዓቱን ምንነት ሊቀይረው አልቻለም፣ውሎ ሳያድር የተሸፈነበት ጭንብሉ በሚሠራው ሥራ እዬተቀደደ ሲመጣ ማንነቱ ታወቀ። ሥልጣኑን ከተቆናጠጠና የሚገለግለባቸውን ተቋማት ከተቆጣጠረ በኋላ እብሪትና ማንአለብኝነቱን ዘርግፎ በአደባባይ ላይ አሰጣው። ያ ሙሴና ነብይ ብሎ አጨብጭቦ የተቀበለው ሕዝብ ኑሮው ከድጡ ወደማጡ ሲሆንበት ቀስ በቀስ ጀርባውን እዬሰጠው ሄደ።በተለይም በአገር ወዳዱ አማራ ተወላጆች ላይ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቀው ጭካኔ ሥጋው ታርዶ ሲበላ፣የማህጸን ውስጥ ጥንስስ ተጎትቶ ለአውሬ ሲጣል፣መነኩሴና ሕጻናት ሲደፈሩ፣ቤተእምነቶቻቸው ሲቃጠሉ፣ሲዘረፉ፣ከኖሩበት ቦታ ሲፈናቀሉ ፣በገነቧት አገር ውስጥ መጤና ሰፋሪ ተብለው ቤታቸው በላያቸው ላይ እዬፈረሰና በእሳት እዬወደመ ጭራሽ እንዳይኖሩ ሲደረግ፣ቤትና አገር አልባ ሲሆኑ ሕግ አከባሪው አማራ ሕግ ያለመስሎት ቢለምንም፣ ቢጠይቅም የሚፈርድበት እንጂ የሚያዳምጠው ጠፋ።ፍትሕ ተረገጠች።ይባስ ብሎ ይህንን ግፍ የተቃወመና ለምን ብሎ የጠዬቀ፣ለፍትሕ የጮኸ ሁሉ ተገደለ፤ታፈነ፤ታሰረ፣ተሰደደ።

ወያኔዎችና ኦነጎች ለተነሱበት ኢትዮጵያን አፍርሶ አገር የማዋለድ ዓላማቸው እንቅፋት ይሆናል ብለው በአንደኛ ደረጃ የፈረጁበት የአማራውን ማህበረሰብ፣መኖሪያ መሬቱን፣የመንጠቅ፣እሴቶቹን በማጥፋት እምነቱን፣ቋንቋና ባሕሉን የመናድ ተልእኮ መንደርደሪያ አድርገው በታሪክ ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ ወንጀል ፈጸሙበት። በየቀኑ የሚደርስበት ወከባ መጠን የለሽ ሆነ። የግፉ ቁና ሞልቶ መፍሰስ ጀመረ። ይህ ነው አማራውን ለትግል ያነሳሳው።

ሁሉን ነገር ችሎ የተኛውን በሬ፣

ነካክተው ነካክተው አደረጉት አውሬ።

አማራው ተረግጦና መብቱን ተገፎ የሚኖርበት ጊዜው እያከተመ ምጥቷል።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለዓመታት በተበታተነ መልኩ ሲታገልና መስዋእት ሲከፍል የኖረው አማራ አሁን ካለፈው ስህተቱ ተምሮ ሃይሉን አስተባብሮ እንደአያት ቅድመአያቶቹ ዱር ቤቴ ብሎ የራሱን የትግል አሰላለፍ ፈጥሮ በፋኖነት የሽምቅ ውጊያ በማድረግ ጠላቶቹን እያርበደበደ መጥቷል።የተደናገጡት ጠላቶቹ ሌባና ዘራፊ፣ሽፍታና ጆቢሳ ብለው ሊያሳንሱት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም።ሁሉም ፋኖ ነኝ እያለ ፊትለፊት ወጥቶ አሳፈራቸው።የተሳለቁበት አሁን ላይ ጀግንነቱን እዬመሰከሩለት መጥተዋል፣መግቢያ ቀዳዳው ጠፍቷቸው ብርክ ላይ ናቸው፣ቀበቶ ብቻ ሳይሆን ሱሪውን እናሶልቀዋለን ያሉት አነጋውያን እራሳቸው ዙሪያው ገደል ሆኖባቸው በሱሪያቸው ላይ እዬቀዘኑ ነው። የአገር መከላከያ ተብዬውን በአገር ሃብት የታጠቀ የጎሰኞቹን ጦር ቢያዘምቱም አልተሳካላቸውም።ከሚዋጋው የሚሞተውና የሚማረከው ዕድል ካገኘ የሚሸሸው በዝቷል።ሸሽቶ ቢሄድ ሞት የሚጠብቀው የኦነግ ጀሌ እጁን መስጠት መርጧል።ፋኖ ባዶ እጁን ሆኖ በድንጋይና በዱላ የኦነግ ጦርን ታንክ፣መድፍ፣ መትረዬስ፣ ዲሽቃና ክላሽ እዬማረከ ጠላቱን በራሱ መሣሪያ እያርበደበደው መጥቷል።ይኸው አገር አጥፊ የጎሰኞች ስርዓት ያገራችንን ድንበር ጥሶ የገባውን የውጭ ወራሪ ያልደፈረውን አዬር ሃይሉን በራሱ ዜጎች ላይ አዝምቶ የቦምብ ናዳ በማዝነብ ንጹሃንን እዬጨፈጨፈ ይገኛል፤የውጭ አገር የዜና አውታሮችና የአንዳንድ አገር የዲፕሎማሲ አካላት ሳይወዱ በግድ አጣመውም ቢሆን እዬዘገቡት ነው።ለዚህ ያበቃቸው በውጭና በውስጥ ተጠናክሮ የመጣው የአገር ወዳዱ ትግልና እንቅስቃሴ እንጂ ወደውና

ስለእውነት ለመቆም ብለው አይደለም።ሁልጊዜም ቢሆን አቅጣጫ እያዩ የሚለዋወጡ እስስቶች ናቸው። ከነዚሁ ጋር የሥርዓቱ ደጋፊና ተከላካይ የነበሩ ግለሰቦችና ስብስቦች እስከዛሬ ድረስ አማራው በግፍ ሲጨፈጨፍ ምንም ያላሉት አሁን ላይ ችግሩ በውይይት ይፈታ የሚል ትርኪምርኪ ማደናገሪያ ይዘው ብቅ ብለዋል።አንዳንዶቹም የሥርዓቱ ደጋፊና አካል የነበሩት በተቃዋሚ ስም ተደራጅተው ለውይይት ለመቅረብ ደፋቀና እያሉ መጥተዋል።በሥልጣን ላይ ካሉት ከግንቦት ሰባት፣ከብአዴንና ከአብን ጎራ የፈለሱ አስመሳዮች እንደለመዱት በመገለባበጥ የሕዝቡን ትግል ለመቀልበስ እንደ ጅብ እዬተጠራሩ ለዳግመኛ ጥፋት ሙከራ በማድረግ ላይ ናቸው።ለፈጸሙት ወንጀል መከላከያ የሚሆን ብልሃት መፍጠራቸው እንደሆነ የማያውቅ ሞኝ አማራ የለም።ፍትሕ ሲሰፍን ሁሉም በሰፈረው ቁና ይሰፈራል እንጂ እንዳለፉት ጊዜያቶች ገዳይ እንደገደለ፣ዘራፊም እንደዘረፈ፣ለሥርዓቱ በጽሑፍም ሆነ በምስል የፕሮፓጋንዳ ድጋፍ የሰጠና በለው ሲል የኖረ ከፍርድ አምልጦ አይኖርም።

እውነተኛ የአማራ ድርጅቶችና የፋኖ ደጋፊዎች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ለመጥለፍና ለማዳከም በዬቦታው የተለያዬ ሰልፍና ስብሰባ እንዲሁም በፋኖ ስም ገንዘብ የመሰብሰብ እሩጫ መኖሩን ታዝበናል። መታወቅ ያለበት ቢኖር የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ተብሎም ተግተልትሎ እንዲገባ እንደማይፈቀድለት ነው።ፋኖ እራሱን ከነዚህ መሰል የጠላት መሳሪያዎች መጠንቀቅ አለበት።ሃይልን ማሰባሰብ በሚል ሽፋን አፍራሾችን በውስጡ እንዲገቡ መፍቀድ አይኖርበትም።ትግል ሊጨናገፍ የሚችለው ከውጭ ጠላት በኩል በሚመጣ ብቻ ሳይሆን ከውስጡ በሚኖሩ አስመሳይ አባሎችም በኩል እንደሆነ መታወቅ አለበት፤ ለዚያም ነው እራስን መመርመርና  በራስ ላይ ዘመቻ ማካሄድ ለትግሉ ውጤት ዋስትና አለው የሚባለው።በጎጥና በመንደር አስተሳሰብ እንዳይጠለፍ ማድረግም አንዱ ዋና የውጤት ወሳኝ እርምጃ ነው።የአገር አጥፊው የብልጽግና አነግ ስብስብ በጥቅም የሚገዛውን ደካማ ሆድ አደር በጥቅም እያሰረ በትግሉ ላይ ማዝመቱን ይቀጥላል። በዚህም የሃይማኖት አባቶች ናቸው በሚል ሽፋን ሻሽ የጠመጠሙ አጭበርባሪዎችን ታቦት እያሸከመ ከኗላቸው የኦነግን ጨፋጫፊ ጦር አስከትሎ ለእርቅና ለሰላም በሚል ዘመቻ ፋኖን ለማጥቃትና  ከማህበረሰቡ ጋር ለመለያዬት ሙከራ አድርጓል፣ፋኖም ይህንን በመገንዘብ በቁጥጥሩ ስር የነበሩትን ቦታዎች በመልቀቅ ለማፈግፈግ ተገዷል። ይህ አይነቱ ድርጊት እንዳይቀጥል ፋኖ ጠበቅ ያለ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል እንላለን።የኦነግ ተላላኪ ሆኖ የመጣ ጳጳስም ሆነ መነኩሴ፣ቄስም ሆነ ዲያቆን ኢማምም ሆነ ሸክ  በአማራው ላይ ግፍ ሲፈጸምበት ድምጹን ያላሰማ  አሁን ላይ አማራው ለሙብቱ ሲነሳ የለም ዝም ብለህ ተገዛ፣ተገደል፣ ተፈናቀል ብሎ የሚመጣውን ተላላኪ  ጠላቱን በሚያስተናግድበት መንገድ ማስተናገድ እንጂ እምነቱ ጋር አያይዞ መመልከት ተገቢ አይደለም።ሕብረተሰቡም በዚህ ተግባር ላይ የተሰለፉ የሃይማኖት ተጠሪዎችን ገለል በሉ ሊላቸውና አክብሮት ሊነፍጋቸው ይገባል።ሃይማኖት የገዳዮች ዋሻ አይደለም።

የሰላም ድርድር ሲሆን ችግሩ ከመፈጠሩ በፊት አለያም የአገር አጥፊዎቹ ሃይል ተሸንፎ መሸነፉን በፊርማ የሚቀበልበት የመጨረሻ እርምጃ እንጂ በትግል መካከል የሚከናወን አይደለም።ፋኖ ያለው ጎሰኛ ሥርዓትና የሚመራበት ድሪቶ ሕገጥፋት ተቀዳዶ እንዲወድቅና በምትኩ ኢትዮጵያን ሰላማዊና ፍትሕ የሰፈነባት የሁሉም ዜጋ መኖሪያ የሚያደርግ ሥርዓት ለመመሥረት ነው።የሕዝቡም ፍላጎት ይኸው ነው።ከዚህ ዝቅ የሚልና የተለዬ  ፍላጎትና ዓላማ የለውም።ታዲያ ከአገር አጥፊውና ለዚህ ዓላማ ተጻራሪ ከሆነው የጎሰኞች ቡድን ጋር በምን ነጥብ ላይ ለመወያዬት ይቻላል?።በምንም።ውይይት ይደረግ ቢባል እንኳን ሁሉም በኢትዮጵያ አንድነት ማመኑን ፣ለዚያ ጠንቅና ለችግሩ መነሻ የሆነው የጎሳ ፖለቲካና ሕገጥፋቱ፣ በጎሳ ተዋረድ የተዘረጋው አገራዊ የክልል አወቃቀሩ መወገድ እንዳለበት፣ ለደረሱት ጥፋቶች ሁሉ ተጠያቂነት መኖሩን በማመንና ጥፋተኞቹን በዝርዝር በማቅረብ ፣ለተጎዱት ካሳ መከፈል እንዳለበት መቀበል  ለውይይቱ ቅድመ-ሁኔታ ሊሆን ይገባዋል።

በሌላም በኩል ከሰሞኑ የተሰማው አስቂኝ የማታለያ ጫጫታ የኦሮሞ ድርጅት ነን ባዮቹም በጁዋር ሞሃመድ በኩል ስለፋኖ ትክክለኛነት መለፍለፍ መጀመራቸው ነው።ይህ ግን ከአንገት በላይ ለማዘናጋት የሚያደርጉት አስመሳይ ጨዋታ ነው።የነሱ የኦሮሙማው ሥርዓት ሌላው ቀርቶ ላለፉት አምስት ዓመታት ያደረገውን ግፍና ጭካኔ፣ ጭፍጨፋና ዘረፋ፣ ማፈናቀልና ግድያ አበጀህ ሲሉ ኖረው አጫሉ ሁንዴሳን ገለው በቀሰቀሱት አመጽ በአንድ ሌሊት ብዙ አማራዎች በሻሼመኒና በሌሎች አካባቢዎች እንዲጨፈጨፉ ማድረጋቸውን የረሳ አማራ ይኖራል ብለው ማሰባቸው የነሱን ጅልነት ፍንትው አድርጎ ያሳያል።በዚች ተራና ኋላቀር ዘዴ አሁን ላይ ውይይት ይደረግ የሚሉትን ወሬ ለምን ይዘው ተነሱ? ብለን ብንጠይቅ አንድም የለውጥ ሃይሉን ጉዞ በመፍራት አለያም በውስጣቸው ያለው የሥልጣን ሽኩቻ በውይይት ሰበብ ይመለስልናል የማለት ተጃጅሎ የማጃጃል ህሳቤ ከመሆን አያልፍም።አሁንም በኦሮሞ ክልል ተብዬው የኦነግ ቄራ አማራዎችና ኦሮሞ ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን እዬተጨፈጨፉ ነው። በዚያ ላይ እንኳን ምንም ትንፍሽ አላሉም።

ከሰሞኑ የታዬው የአገር መፍረስ ሂደትና የሕግ አለመኖር በፓርላማ ተብዬው የጎሰኞች በረት ውስጥ የተላለፈው ውሳኔ ነው።በጣም የሚገርመውና ሥርዓቱንና ባለሥልጣናቱን ይበልጥ የሚያጋልጠው አንድ የአገር ፓርላማ ነኝ የሚል ተቋም በራሱ ሕዝብ ላይ የጦርነት አዋጅ ማወጁ ነው። በተለይም ጦርነት የታወጀበት የአማራው ተወላጅ እራሱ መርጦ በላካቸው ከመቶ ሰላሳ በላይ በሆኑት ወኪሎቹ ሲካድና በአውሮፕላን ቦምብ፣ታንክና መድፍ እንዲደበደብ ሲፈረድበት መደገፍና፣ ማዬትን የመሰለ የሚዘገንን ነገር የለም።ህሊናን ሆድ ይጋርደዋል ማለት እንዲህ ነው። በፓርላማ ውስጥ ከተቀመጡት ከ547 ሰዎች መካከል 16 ቱ ብቻ አዋጁን ሲቃወሙ 12ቱ ደግሞ ሁለት እግራቸውን አንፈራጠው ድምጽ ለመስጠት አለመፈለጋቸው ታውቋል፤ይህ ማለት ያሻህን አድርግ አያገባኝም ማለት ነው። ያልተገነዘቡት ቢኖር ለሥርዓቱ ድጋፍ አለመስጠታቸው ለጥቃት እንደሚያጋልጣቸው ነው። የፓርላማው አባላት ይህ የጎሳ ስርዓት ከተወገደ ያገኙት ጥቅም ማለትም ከፍተኛ ደመወዝ፣ነጻ መኖሪያ ቤትና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም ሊቀርባቸው ስለሚችል ያንን ላለማጣት ሲሉ ከሥርዓቱ ጋር አብሮ መበስበሱን መርጠዋል።ከነዚያ ውስጥ ለሥርዓቱ የመጥረቢያው እጀታ ሆነው ሲያገለግሉ የኖሩት ባእዴኖችና አብኖች እንዲሁም ሌሎቹ በዚህ ደረጃ ላይ ወርደው ሲገኙ በታሪክ የሚፈረድባቸው መሆኑ ብቻም ሳይሆን ለተዋለዳቸውና ለተዛመዳቸው የዘላለም ሃፍረት ነው።አንዳንዶቹ አዋጁን ቢቃወሙም ሄደው ሄደው ችግሩ በውይይት ይፈታ የሚል እራስን የማዳኛ ሃሳብ ሲናገሩ ተሰምቷል።ከነዚያም ውስጥ አንዱ ገዱ አንዳርጋቸው የተባለው ጉድ ነው።አማራውን በወያኔ ገመድ ተብትቦ ፣መሬቱን አሳልፎ የሰጠ ይህ ወንጀለኛ ዛሬ ከመሸ ተነስቶ ለአማራ ተቆርቋሪ መስሎ መውጣቱ የሥርዓቱ ጸሃይ እዬጠለቀች መምጣቷን ያሳያል።የሥርዓቱን ወንጀል ማጋለጡ እንደምስክር ቢያስቆጥረውም እራሱን ከወንጀሉ ነጻ አያደርገውም ፤ምናልባት ሊጣልበት ከሚገባው ቅጣት ላይ ትንሽ አስተያዬት ሊደረግለት ይችል ይሆናል።80 ጅራፍና ዕድሜ ልክ እስራት ይጣልበት ቢባል በ60 ጅራፍና በ50 ዓመት እስራት ይቀጣ በሚል ሊቃለልለት ይችል ይሆናል።ያንን ውሳኔ የሚሰጠው ግን የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ይሆናል።

አማራውን በሃይል ብቻ ሳይሆን በምጣኔ ሃብትም ለማንበርከክ ብዙ እቅድ ወጥቶ ተግባራዊ እዬሆነ ነው።የአማራ ባለሃብቶች ገንዘባቸውን እንዳያንቀሳቅሱ ቁጥጥር እንዲደረግባቸውና የክልሉም ካዝና በሁለት የኦነግ ታማኝ ተላላኪዎች በሰማ ጥሩነህና በጥላሁን ማረ በጋራ ፊርማና ውሳኔ ካልሆነ በቀር እንዳይንቀሳቀስ ተወስኗል።ከእራቡና ከጥማቱ ጋር በተጨማሪ ኮሌራና ኩፍኝም የብዙ ሕጻናትን ሕይወት በመቅጨት ላይ ናቸው።

ትግሉ እየመረረ ሲሄድና ፋኖ እያሸነፈ ሲመጣ ሥርዓቱ የመጨረሻውን ለማድረግ ከንዱን ከመዘርጋት እንደማይቆጠብ መታወቅ አለበት።የቆሰለ ነብር ወይም ተስፋ የቆረጠ ሽፍታ የሞት የሽረት ሃይሉን ይጠቀማል። የሕዝባዊ ትግሉም ጎራ እንዲሁ ለወሳኙ ፍልሚያ እራሱን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።ብረት እንደጋለ ነውና ጠላትን ፋታ ሊሰጠው አይገባም።ለአገር አንድነት ለእኩልነትና ለሰብአዊነት የሚቆም ሁሉ ከአማራ ፋኖ ጎን ሊቆም ይገባዋል።ይህ ትግል ከተዳከመ ለዘለዓለም ባርነት ፈቃደኛ መሆን ማለት ብቻም ሳይሆን አገር አልባ ሆኖ ተሰዶ መኖር ማለት ነው።፣ሁሉም ለትግሉ የሚችለውን ያበርክት፣ ይቀላቀል ፣በጦር ሜዳ ይሰለፍ፣ለሕዝባዊ ሃይሉ ለፋኖ የሚያስፈልገውን ሁሉ ያበርክት።አንድ ማእከል በመፍጠር እርዳታውንና ተሳትፎውን ያጠናክር።አማራ አንድ ነው፣የመከላከያ ሃይሉ ፋኖም አንድ ነው።ለመከፋፈል የሚዳርጉ እንቅፋቶችና መንገዶች ጥርቅም ብለው መዘጋት አለባቸው።

በዬማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ለውጥ ፈላጊ እዳር ቆሞ መታዘብ ሳይሆን የትግሉ አካል ሊሆን ይገባዋል።ኢትዮጵያ የአማራው ብቻ አይደለችም፣አማራው የሚታገለውም ትግል ለእራሱ ብቻ ሳይሆን ከህልውናው ጋር ለተቆራኘው ኢትዮጵያዊነት ነው።ኢትዮጵያዊነቱም ከሌላው ወገኑ ጋር ብዙ መስተጋብሮች አስተሳስረውት የአንድ አገር ዜጋም ብቻ ሳይሆን በመዋለድ በእትብት የተሳሰረ ቤተሰብ አድርጎታል።በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የአማራው የትውልድ ሃረግ አላቸው። በአማራው ላይ የሚደርስ ጥቃት በነዚህም ላይ የደረሰ ጥቃት ሆኖ መወሰድ አለበት፤ይህንንም በገሃድ እያዬነው ነው። ስሙ እዬታዬ፣ከልስ እዬተባለ የሥራና የትምህርት ዕድል የሚነፈገውን ቤቱ ይቁጠረው።ለእውነትና ለፍትሕ ለመቆም ከአማራ መወለድ አያስፈልግም፤ሰው መሆን ብቻ ይበቃል። የወላይታው አቶ ታዲዎስ ታንቱ፣የትግራዩ አቶ ጌታቸው ረዳ፣የጋምቤላው አቶ አባንግ ሜቶ፣ የሌሎቹም አሰላለፍና መከራ ማዬት የዚያ ምስክር ነው።የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ነዋሪ ሕዝብም በአማራው ላይ የሚደረገውን ጭፍጨፋና በደል ተቃውሞ መግለጫ አውጥቷል።በአንጻሩ ደግሞ አማራ ሆኖ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለጨፍጫፊው ሥርዓት መሣሪያ በመሆን ሽርጉድ የሚል፣የሚገል፣ የሚያሳድድና የሚወነጅለውን የአማራ ተወላጅ ሲያዩት ምነው ባይበላስ ቢቀር ያሰኛል። ዱሮስ እዬሱስን የሰቀሉት የራሱ ጎሳዎች አይሁዶች አይደሉምን?

ከሰሞኑ በዳንኤል ክብረት ላይ ግድያ ተሞከረ የሚል ወሬ ብቅ ብሎ ሳይደገም ጠፍቷል።ቦታውና ሰዓቱ አለመገለጹም ሌላው አጠያያቂ ጉዳይ ነው።ይህንን ያነሳነው በሰውዬው ላይ የተደረገው ሙከራ አሳዝኖን ሳይሆን የአብይ አህመድ ተንኮል ከዚህ ጋር የተያያዘ ሊሆን እንደሚችል ወይም በኦነጎች አለያም በወያኔዎች ሊወሰድ የሚችል እርምጃ እንጂ ፋኖ ይህንን የቁም ሙት ለመግደል ጥይት ያባክናል ብለን አናስብም።በሰውዬው አድር ባይነትና በሚሰራው ክህደት የተነሳ አንድ አንጀቱ ያረረ ግለሰብም የወሰደው እርምጃ ሊሆን ይችላል።ፋኖ ግን ፊትለፊት መሣሪያ አንግቦ የመጣውን ይገላል፤የማረካቸውን እንኳን በሰው ደረጃ ይዞ እንደጥፋታቸው መክሮ መሣሪያቸውን አስረክበው ወደፈለጉበት እንዲሄዱ ያደርጋል።በአገር ላይ ክህደትና በሕዝቡ ላይ በደል የፈጸሙትን ባለሥልጣኖች እጅ ከፍንጅ ይዞ ለፍርድ ለማቅረብ ይፈልጋል እንጂ በተኩስ አስደንግጦ አይመለስም።ምርጫ ካጣና ግድ ከሆነበት በተጠና መንገድ የማያዳግም እርምጃ ለመውሰድ ይገደዳል።ይህ ለፍትሕ የሚታገል የሕዝባዊ ጦር ዋና መገለጫው ነው።

ሌላው የአብይ አህመድ የሰሞኑ ትያትር የኢሚራቱን መሪ ሸኪ ሞሃመድ ቢን ዛይድን በመጋበዝ የጋለ አቀባበል ማድረጉ ነው።ሸኩ እንደማንኛውም አገር መሪ ለአገሩ ጥቅም በሚያዋጣው መንገድ ከአገራቶች ጋር ግንኙነትና ውል ይፈራረማል።በኢትዮጵያም ውስጥ መጠነ ሰፊ እቅዶችን በመዘርጋት ብዙ ቢሊዮን ዶላር አፍሷል።የኢትዮጵያ ሕዝብ በማያውቀው መልኩ ትልቁን የባለቤትነት ድርሻ መያዙ ባይገለጽም የሚያስጠረጥሩ ሁኔታዎች ጎልተው ይታያሉ።አብይ አህመድ ያለበትን የዶላር እጥረት

የሚያካክሰው ከነዚሁ አይነቶቹ መሪዎች ጋር በእስከጀርባ በሚያደርገው ስምምነት ነው።እንኳንስ ሕዝቡ ፓርላማ ተብዬውም የማወቅ መብትም ሆነ የመጠዬቅ ድፍረት የለውም።አገራችን የመጨረሻ እጣዋ ሁሉም ባወጣው ገንዘብ ልክ የሚገባውን ድርሻ ቦጫጭቆ የምትፈርስ አገር መሆኗ ነው።ያንን የሚያስቆም ሕዝባዊ ሃይሉ ካልተጠናከረ በስተቀር ሌላ መፍትሔ አይኖርም።ለዚያም ነው ሕዝባዊ የፋኖ ጦር ይደራጅ፣ይጠናከር፤አገር ወዳዱ ተሰባስቦ አገሩን ለማዳን የሽግግር መንግሥት ያቋቁም የምንለው።

በመጨረሻም ልናሳስብ የምንወደው በውጭ አገር የሚኖረው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ስንዴውን ከእንክርዳዱ ለይቶ እራሱን በማደራጀት ለአገርቤቱ ሕዝባዊ ትግል አጋርነቱን እንዲገልጽና የሚያስፈልገውን  የገንዘብ ዕርዳታ በአንድ አሰባሳቢ አካል በኩል  እንዲያበረክት ነው።በተጨማሪም በሚኖርበት የተለያዩ አገሮች ለመንግሥታትና የመብት ተሟጋች ድርጅቶች ሁኔታውን በማስረዳት ሌላው ቢቀር ለአገር አጥፊውና ለጎሰኛው የኦነግ መራሹ የአብይ አህመድ መንግሥት ድጋፍ እንዳይሰጡና ወንጀለኞች ለዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ጥያቄ የማቅረብ ዘመቻው ተቀናጅቶ እንዲቀጥል ነው።

ድል ለሕዝባዊ ትግሉ

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!